**ለፕሮፌሰር መሥፍን የመጽሐፍ ምረቃ ታዳሚዎች እና ለእርሳቸው አድናቂዎች  በሙሉ፣**

ፕሮፌሰሩ በወዳጆቻቸው አማካኝነት «አዳፍኔ» ብለው የሰየሙትን መጽሐፋቸውን ለመሸጥ ዋሽንግተን ዲሲ ሴብተምበር 13 ቀን 2015 መጽሐፉን እንደሚያስተዋውቁ ማስታወቂያ ተነግሯል። በዚህ ስብሰባ ላይ የምትገኙ ኢትዮጵያውን በተለይም የዐማራው ነገድ አባሎች ፕሮፌሰሩን የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንድትጠይቁልኝ አበክሬ እጠይቃለሁ።

ተክሌ የሻው፣

ፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም፡-

***«ሥልጣን፣ ባህልና አገዛዝ፤ ፖለቲካዊ ምርጫ» በሚል ርዕስ በ2003 ባሳተሙት መጽሐፉዎ ገጽ 120 ላይ  እንዲህ ብለዋል።***

***«ኅዳር 1951 ዓም ከአጼ ኃይለሥላሴ ጀምሮ እስከ ታላላቆቹ ባለሥልጣኖች ባሰራጩሁት የጥናት ጽሑፍ ስለኢጋዴን የሚከተለውን ብየ ነበር።***
***«በጠቅላላው የአማሮቹና የሱማሌዎቹን ግንኙነት ላስተዋለው፣ አማራዎቹ የሚያሳዩት የበላይነት መንፈስና በሱማሌዎቹ ላይ ያላቸው ንቀት፤ ሱማሌዎቹ በበኩላቸው ያላቸው ኩራት በአማራዎቹ ንቀት እየተነካባቸው የሚሰማቸው ስሜት በአንዴ ይታወቃል። ''ቆሻሻ ሱማሌ''በያለበት የሚሰማ ነው። በዕድሜም ሆነ በክብር ከፍ ያሉትን ሱማሌዎች እርሰዎ እያለ የሚያነጋግራቸው በቁጥር ነው።---እንደዚህ ዓይነቱ የሌለውን የአማራ የበላይነትና የሱማሌ የበታችነት በግልጽም በድብቅም የሚያሳይ መንፈስ የሱማሌዎቹን ልብ በጣም እንደሚያምክረው የሚያጠራጥር አይደለም።  ሱማሌዎቹ ልክ እንደአማራዎቹ መሆናቸውን ሁሉ የተገነዘቡት አይመስሉም፤ ሱማሌዎቹም ሁሉ የሚውቁት አይደለም።»***

ወደ ጥያቄው በቀጥታ ከመገባቱ በፊት በዚህ ጽሑፉዎ «--እንደዚህ አይነቱ *የሌለውን የአማራ የበላይነትና የሶማሌ የበታችነት* በግልጽም በድብቅም የሚሳይ መንፈስ የሱማሌዎቹን ልብ በጣም **እንደሚያሞክረው** የሚያጠራጥር አይደለም። የሚል ሀሳብ ሰፍሯል። ይህ ዐረፍተነገር ምን ለማለት የተቋጨ  እንደሆነ ለመረዳት ያስቸግራል። የመጀመሪያው አስቸጋሪ የሚያደርገው «**እንደሚያሞክረው**» የሚለው ቃል ፍች ግልጽ አለመሆኑ ነው። ይህ ቃል «እንደሚያሻክረው» ለማለት ታስቦ ከሆነ ትርጉም ይሰጣል። ካልሆነ ቃሉ ትርጉም ያሻዋል። ያም ሆኖ፣ **«የሌለውን የአማራ የበላይነትና የሶማሊያ የበታችነት»** የሚለው ሐረግ ከላይ የተነደረደሩበትን አማራው በሱማሌዎች ላይ የበላይነቱን ፣ንቀቱን  ያሳያል፣ ያንቋሽሻል ሲሉ የዘረዘሩትን የሚሽር ነው። ዕውነታውም በሁለቱ ነገዶች መካከል ያውም ኦጋዴ ዐማራው ፈርቶና ተሸማቆ ከሚኖርበት አካባቢ ቀርቶ በሌሎች ላይም የበላይነኝ ያለበትን በመረጃ አሳማኝ በሆነ መልኩ ማያሳያ የለም። የእርሰዎም ጥናት ያሉ ጥናቱ እንዴት እንደተጠናና ከዚያ መደምደሚያም ላይ ለመድረስ እንደተቻለ የሚያሳይ ነገር የቀረበ ባለመሆኑ ዕውነት ነው ብሎ ለመቀበል ያስቸግራል። እርሰዎ እንዳሉት «መንፈስ» ፣«ስሜት» ነው። ይህ ደግሞ ተጨባጭ አይደለምና ታማኒነት የለውም። ስሜትና መንፈስ የሚባሉት ቃላቶች ብሔርተኞች  ነገዳቸውን በዙሪያቸው ለማሰባሰብ የሚጠቀሙባቸው የስስ ስሜት መገለጫዎች ናቸውና! የእርሰዎም ከዚህ የጠራ ሆኖ ባለመቅረቡ ጥላቻን ከመግለጽ ያለፈ፣ ሰዎችን ሊያሳምን አይችልም። ብሔርተኛ ሱማሌዎችን ግን ዐማራ ጠላታችን ነው፤ ይንቀናል፣ ይሰድበናል ብለው ነገዳቸውን እንዲሰበስቡ እርሰዎ ታላቅ መሣሪያ ያቀበሏቸው መሆኑን ገልጸውልናል። ለዚህም ነው ዐማራው ሲያልቅ ስለዐማራው በመጮህ ፋንታ የለም እያሉ የሚጪሁት። ዛሬ የለም ያሉት ዐማራ ያን ጊዜ በ1951 እና በዚህ መጻፈዎ በ2003 ከየት መጥቶና አገኝተውት ነው ዐማራ ሱማሌን ይንቃል ያሉት በማለት የገለጹዋቸው ጉዳዮች ሠፊ ማብራሪያ ይጠይቃሉና ማብራሪያ እንዲሰጡባቸው ይጠየቁ።

ከዚህ በተረፈ የሚከተሉትን ጥያቄዎች እንዲጠየቁ  አቅርቤአለሁ።

**ጥያቄዎች፡-**

1. በ1951 ለንጉሡና ለባለሥልጣናቱ በዐማራዎቹና በሱማሌዎቹ መካከል አለ ብለው ላቀረቡት የበላይና የበታችነት ስሜት ከንጉሡም ሆነ ከባለሥልጣናቱ የተሰጠዎ መልስ ነበር ወይ? ከሆነስ መልሱ ምን የሚል ነበር?
2. ዐማራዎቹ በሱማሌዎቹ ላይ ያሳያሉ ስላሉት ንቀት ፣ በምርምር ላይ ያረጋገጡት ሳይንሳዊ ማረጋገጫ ምንድን ነው? በኦጋዴን ስንት ዐማታዎች ይኖሩ ነበር? ምንስ የኢኮኖሚ ተቋሞችን ዐማራዎቹ ይዘው ነበር? የአውራጃና የወረዳ አስተዳዳሪዎቹ እነማን ነበሩ? የዐማራው የበላይነት፤ የሱማሌዎቹ የበታችነት ቁሣዊ መገለጫዎቹ ምንድን ነበሩ?  ዐማራ ያሏቸ ው አማርኛ በመናገራቸው ወይስ ዘራቸውን ጠይቀው አረጋግጠው? በዚያን ጊዜ የኢጋዴን ነዋሪዎች የነገዶች ሥብጥርና አሠፋፈር ምን ይመስል ነበር?
3. አንድ ሰው ተነስቶ ሌላውን ሲሰድብ ብንሰማ ፣ሰዳቢውም ሆነ ተሰዳቢው የየነገዳቸው ተወካዮች አድርጎ ማቅረብ ይቻላል ወይ? ከተቻለ እንዴት?

4. ስንት ዐማራ «ቆሻሻ ሱማሌ» እያለ ሲሳደብ ተሰማ? ቆሻሻነት የንጽሕና ጉድለትን እንጂ፣ የነገድን መቆሸሽ ያመለክታል ወይ? የቆሸሸ የማንኛውም ነገድ ተወላጅ ፣መቆሸሹን ያዬ የሌላ ነገድ ሰው ቆሻሻ ቢለው ነገዱን እንዳለ ተሳደበ ማለት ይቻላል ወይ?
5. በሱማሌ ቋንቋና ባህል ታላላቆችንና ባለሥልጣኖችን በአክብሮት መጥራት ይቻላል ወይ? የቋንቋው ሥርዓት ይፈቅዳል ወይ? ይህ ከሌለ ዐማራው ለምን አንቱ ይላል? ስም የሚወጣው ከቤት ነው። ጎረቤት መከተል ነው። የነገዱ አባል፣ አንተ እያለ የሚጠራውን ሌላው በምን ምክንያት አክብሮ እንዲጠራው ይጠበቃል?
6. ሱማሌዎች ኢትዮጵያዊ መሆናቸውን፣አማራዎች አለመገንዘባቸው፣በሱማሌዎቹም ይኸው መንጸባረቁ ሲሉ የገለጹት እንደሚሉት ተንጸባርቆ ከሆነ ችግሩ የዐማራ የበላይነት ወይም የሱማሌ የበታችነት ስሜት የፈጠረው ነው? ወይስ መሃይምነት? መሃይምነት ከሆነ ደግሞ ይህን መዋጋት ያለበት የተማረው እንደርሰዎ ያለው አዕደለም ይላሉ?
7. እርሰዎ ይኸን በኦጋዴን፣ በሶማሌና በዐማራው መካከል ያለውን ልዩነት ተገንዝበው ከመጡ በኋላ፣ እንደዚህ ያሉ ችግሮችን እንዲፈቱ፣ ንጉሠ-ነገሥቱ የአውራጃ አስተዳዳሪ አድርገው ሲሾሙዎ ያን ተቀብለው ይህን ዓይነቱን ችግሮች ለማስተካከል ለምን አልፈለጉም? ሠርተው ከማሳየት ፋንታ ለምን መተቸትን ምርጫ አድርገው ያዙ? የአውራጃ ገዥነቱን ኃላፊነት ለምን አልቀበልም አሉ?
8. በ1951 ይህን ዐማራ ሱማሌን ይንቃል፣ ያዋርዳል ያሉትን ሲጽፉ ፤ሱማሌዎች በዐማራው ላይ የዘር ጥላቻ እንዲኖራቸውና ዛሬ ከሶማሊያ ክልል ዐማራ በገፍ እንዲባረር ለበቃው ድርጊት እርሰዎ አስተዋጽኦ አላደረኩም ይላሉ? ይህንም ከግምሽ ምዕተ ዓመት በኋላ እንዲህ ብየ ነበር ብለው ደግመው መጻፈዎ ዐማራውን ሁሉም እንዲያጠፋው በትር እያቀበሉ መሆኑን እንዴት አልተገነዘቡም?
9. ዐማራ የለም በማለት ደጋግመው ሲናገሩ ተደምጠዋል። ዐማራ የለም የሚሉት በባህል እንጂ፣ በዘር የለም ነው የሚሉት? ይህ ከሆነ ኦሮሞ፣ትግሬ፣ጉራጌ ወዘተ ከዚህ በምን ይለያሉ?
10. ዐማሮች ይውጡ እየተባሉ ከየቦታው የሚባረሩት አባራሪዎቹም ዐማራዎች ናቸው፤ ተባራሪዎቹም ዐማራ ነን እያሉ ነው፤ ባይኖሩ ይሻል ነበር፤ አይገደሉም ነበርና! የተገደሉት እነማን ናቸው?
11. ዐማራ የለም ይላሉ፤ አንድ ሰው እኔ ዐማራ ነኝ ቢለዎ ምን ይሉታል? አይደለህም ማለት ይቻላል?